የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፶፭
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 55
ADDIS ABABA- 30th June. 2005

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፭/፲፱፻፺፯ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ/ማሻሻያ/ አዋጅ ገጽ ፫ሺ፩፻፸፬

CONTENTS

Proclamation No. 465/2005

Definition of powers and duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (Amendment) Proclamation Page 3174

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፭/፲፱፻፺፯

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ማሻሻል ስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፭/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### ፪. ማሻሻያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ /፱/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፱/ ተተክቷል፣

## PROCLAMATION NO. 465/2005.

## A PROCLAMATION TO AMEND THE DEFINITION OF POWERS AND DUTIES OF THE EXECUTIVE ORGANS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA PROCLAMATION

**WHEREAS**, it has become necessary to amend the Proclamation providing for the definition of powers and duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Definition of powers and duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (Amendment) Proclamation No. 465/2005".

### 2. Amendment

Sub-Article (9) of Article 23 of the definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 (as amended) is deleted and replaced by the following new Sub-Article (9):

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

"፱/ ዓላማቸው ትርፍ ማግኘት ያልሆኑ የውጭ ድርጅቶችን እንዲሁም እንቅስቃሴያቸው በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች የሆነ ወይም አንድ ክልል ያልወሰነ የአገር ውስጥ ድርጅቶችንና ማኅበሮችን ይመዘግባል፣"

## ፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት



"9/ Register non-profit making foreign organizations, and local organizations and associations operating in Addis Ababa and Dire Dawa cities or more than one regional states,"

## 3. Effective Date

The Proclamation shall enter into force on the 30th day of June, 2005.

**Done at Addis Ababa, the30th day of June, 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት